**ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ**

**የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ**

**የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል**


**በ**


**በሬሳ መርጋ**


# “በ ወለጋ ጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ የ ነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር”


ሰኔ 2014 አ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ

የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

በ

በሬሳ መርጋ

የጥናቱ አማካሪ

ሳራ መሀመድ

ለቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት
የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ

የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ሰኔ/ 2014 ዓ .ም

# የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፁሁፍ በወልቂጤ ዩነቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆነን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም__________________________________

ፊርማ__________________________________________

ይህ ጥናት በተማሪ በሬሳ መርጋ በወለጋ ጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ የ ነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስርአት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር የመጀመርያ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፁሁፍ ሲሆን የዩንቨርስቲዉ ጥራት ደረጃ የሚላና በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆነን ማረጋገጫ ነዉ።

ፈታኝ አንድ______________________________________ፊርማ

ፈታኝ ሁለት_____________________________________ፊርማ

ቀን________________________

# ምስጋና

በቅድሚያ ምስጋናዬ የሚሆነው ሳላውቅ ያወቀኝ ሳልወደው ነፍሱን ሰቶ የፍቅርን ትርጉም ያስተማረኝ ለእግዚአብሔር ልጅ ለክርስቶስ ይሁንልኝ ። ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ሀሳቤን ተረድታ እናታዊ ምክሯን እየለገሰች ጥናታዊ ፅሁፌ ያማረ እንዲሆን ለረዳቺኝ ለመምህሬ ለሳራ መሐመድ አመሰግናለሁ። እንዲሁም በሚያስፈልገኝ እርዳታ ሁሉ ከጎኔ የነበሩ የዘሩት ፍሬ አብቦ ለማየት የታደሉትን አባቴ መርጋ ገመዳ እና እናቴ እመቤት አበራ ከልብ አመሰግናለሁ ።

# አበርክቶ

ቅድመ አያቶቻችን ይህንን ክንዋኔ ሲተገብሩ ቆይተው ለኛ አስተላልፈዋልና የዚህ ዘመን ትውልዶች ስለዘነጉት ባህሉ ለሚመለከታቸው ሁሉ ይሁንልኝ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያተኩረው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሆሮ ጉድሩ ዞን በጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር እና የነቀተኒ ክንዋኔዎችን በማዋሀድ ትውፊታዊ ይዘቱን እና ከተውኔት አላባውያን ጋር ያለውን ጥምረት መተንተን ነው። አጥኚ ለጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን ይጠቀማል ። የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት በሚከወንበት ሂደት ውስጥ የቃላት ምልልስ (ቃለ ተውኔት) ፣ አልባሳት ፣ ምርቃት ፣ ቁሳቁስ ፣ የመከወኛ ቦታ (መቼት) ፣ ዘፈን ፣ ውዝዋዜ ፣ በአጠቃላይ ስለ ባህሉ ከትውፊታዊ ተውኔት ጋር በማጣመር ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሀፍትን እና ተዛማጅ ፅሁፎችን በመዳሰስ እንዲሁም ምልከታ እና መዛግብትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አድርጎ በመጠቀም ይህ ጥናት ትንታኔ ሰጥቷል ።

## ሙዳየ ቃላት

ሰበት መሪ(sabat marii) ...............................ሴትን ልጅ በጋብቻ ለመውሰድ የሚደረግ የመጨረሻ አማራጭ ::

ቡቲ(butii) ....................................................ጠለፋ

ጀቢ ሆቱ(jabbi hootuu)................................የአክስት ልጅ

ጎንዶ ቦሬ(gundoo boree) ...........................ሰፌድ

ኡልማ ኢይ(ulumayii) ..................................የሚሸት ቅጠል

ኦኮቴ(ookkotee)...........................................እንስራ

ጎዶ(goodo) .................................................ጫጉላ

## ማዉጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና……………………………………………………………………………1

አበርክቶ…………………………………………………………………………….1

አጠቃሎ……………………………………………………………………………1

1 መግቢያ ........................................................................................................1

1.1የጥናቱ ዳራ.....................................................................................................1

1.2የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..................................................................................1

1.3የጥናቱ አላማ.................................................................................................2

1.3.1የጥናቱ አብይ አላማ........................................................................................2

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ.......................................................................................2

1.4ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች...........................................................................2

1.5የጥናቱ ጠቀሜታ.............................................................................................2

1.6የጥናቱ ዘዴ.....................................................................................................2

1.6.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ .....................................................................3

1.6.1.1 መዛግብት ..................................................................................................4

1.6.1.2 ምልከታ ....................................................................................................4

1.7የጥናቱ ወሰን..........................................................................................................5

1.8የጥናቱ አደረጃጀት....................................................................................................5

ምእራፍ ሁለት………………………………………………………………………………5

2 ክለሳ ድርሳናት……………………………………………………………..…………5

2.1 የትዉፊት ምንነት……………………………………………………….………5

2.1.1 የትዉፊታዊ ተዉኔት ምንነት………………………………………………………5

2.1.2 የትዉፊታዊ ተዉኔት መገለጫ ባህሪያት……………………………..……………5

2.2 የትዉፊታዊ ተዉኔት ኣለባዉያን…………………………………..…………7

2.2.1 ቃለ ተዉኔት………………………………………………………..……………7

2.2.2 መቼት…………………………………………………………..………………..8

2.2.3 የሚና ክፍፍል………………………………………………………….……..9

2.2.4 ቁሳቁስ…………………………………………………………..…………..9

2.2.5 አልባሳት……………………………..………………………………..……..10

2.2.6 ከዋኞች……………………………..………………………………………..10

2.2.7 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት………………………………………………………11

ምዕራፍ ሶስት…………………………………………………………..…..……12

3.1. የነቀተኒ ምንነት……………………………….........................……..12

3.2 የነቀተኒ የሰርግ ስነ-ስርዓት ከትውፊታዊ ተውኔት አለባውያን አንፃር……………………13

3.2.1 ከመቼት አንፃር…………………………………………………………………13

3.2.2 ከድርጊት አንፃር…………………………………,,,,,,,,,,,,,,,,,,,……………13

3.2.2.1 ቅድመ ክንውን…………………………..……………………..………13

3.2.2.2. በክዋኔው ወቅት……………………..…………………………..……..15

3.2.2.3 ድህረ-ክዋኔ……………………………..………………………..……16

3.2.3ከቃለ- ተውኔት አንፃር……………………………..………………………….....…..….17

3.2.4 ከአልባሳት አንፃር………………………………..………………………………20

3.2.5 ከቁሳቁስ አንፃር………………………………………..…………………,,…….21

3.2.6 ከሚና ክፍፍል አንፃር………………………………………..……………..………23

ምዕራፍ አራት……………………………………………………………..……………..25

4.1 ማጠቃለያ …………………………………………………..………………..….…….25

4.2 የመፍትሔ ሀሳቦች …..…………………………………………..……..……...……….25

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው……………………………………………..………………………26

ዋቢ ጽሁፎች…………………………………………………………..…………..…...…. 28

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ኢትዮጵያ ከ 80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦች የሚኖሩባት ህብረ ብሄራዊት ሀገር ነች።እነዚህ ህዝቦችም ኢትዮጵያ ማንነታቸው ደምቆና ተዉቦ አንደኛው ከሌላኛው ጋር በባህላቸዉ እና በታሪካቸዉ ተሳስረው ለዘመናት አብረው የኖሩ ናቸው።እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህል ቢኖራቸዉም አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩበት የራሳቸዉ መገለጫዎች ወይም እሴቶች አሏቸዉ። በመካከላቸዉ የባህል መወራረስ(መመሳሰል) ቢኖርም እንደ ክንዋኔዉ ይዘትና ሁኔታ ያለዉን ልዩነት በመቻቻል በልዩነት ዉስጥ አንድነት ፈጥሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ለዘመናት ተሰብስበዉ እና ተከባብረዉ ይኖራሉ። ከነዚህም ህዝቦች መካከል በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በወለጋ ሆሮጉድሩ ዞን የሚገኙት የጀርደገ ጃርቴ ወረዳ ማህበረሰብ ተጠቃሾች ናችሁ።እነዚህ ማህበረሰቦችም እንደ ሌሎቹ የራሳቸዉ የሆነ ባህል፣ ወግ፣ታሪክ፣ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች የአኗኗር ስርአት አላቸው።በ ማህበራዊ ህይወታቸው የሚያከናዉኗቸዉ ትዉፊታዊ ክንዋኔዎች መካከል ሀይማኖታዊ ስረአቶች፣ የለቅሶ ስርአቶች ፣ የሰርግ ስነ ስርአት እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።የሰርግ ሰነ ስርዓታቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ማህበረሰቡ ይገለገልበታል። አራት አይነት ከሆኑት የወለጋ ጃርደጋ ጃርቴ የሰርግ ስነ ስርአቶች መካከል አጥኚው የነቀተኒ የጋብቻ ስርአት ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዉ በወልቂጤ ዩንቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል በትምህርት ቆይታዉ ትዉፊታዊ ቴአትር የተባለዉን ኮርስ በወሰደበት ጊዜ ስለ ትዉፊታዊ ተውኔት ግንዛቤ ስለጨበጠ ብሎም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በወለጋ ሆሮ ጉድሩ ዞን የጃርደገ ጃርቴ ተወላጅ በመሆኑ በትምህርቱ ያገኛቸዉን እዉቀት መሰረት በማድረግ ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተወራረሰ የመጣበትን መንገድ በጥናት የተደገፈ መረጃ ለማስቀመጥ፤እንዲሁም ክንዋኔዎቹን ከትዉፊታዊ ተውኔት አላባዉያን አንፃር መተንተን።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ የነቀተኒ የሰርግ ስነ ስርአትን ከትዉፊታዊ ተውኔት አላባዉያን አንፃር መተንተን ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓትን ከአልባሳት አንፃር መተንተን
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስረአት የመከወኛ ቦታውን (መቼት) መግለፅ
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት በክዋኔ ጊዜ የቁሳቁስን ፋይዳ ማሳወቅ
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት ቅደም ተከተላዊ ሂደቶችን መተንተን
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት የሚና ክፍፍልን መግለፅ

## 1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸችዉ ጥያቂዎች

- ነቀተኒ ምንድነው?
- የነቀታኒ የሰርግ ስነ ስርአት ምን ይመስላል?
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን ጋር ያለው ተዛማጅነት ምን ይመስላል?
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስረአት ለማሕበረሰቡ ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?
- የነቀተኒ የጋብቻ ስረአት ከሌሎቹ የሰርግ ስረአቶች በምን ይለያል?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል፡፡

- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓት ባህሉን እየዘነጉት ለሚገኙ የማህበረሰቡ ክፍሎች እንዲሁም ባህሉን ማወቅ ለሚፈልጉ አካላት ያልተሸረፈውን እምቅ የሆነውን ትውፊታዊ ይዘቱን ማስገንዘብ ፡፡
- የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓት ወደ ትውፊታዊ ተውኔት መቀየር ለሚፈልጉ እንደ መነሻ ይጠቀሙበታል፡፡

- ሌሎች የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ባህሎች እንዲተዋወቁ ይህ ጥናት እንደ ምሳሌ ያገለግላል፡፡
- የነቀተኒን የሰርግ ስነስርዓትን ትውልድ እንዲማርበት ማድረግ እና ስለ ባህሉ መረጃ ለማስቀመጥ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ዘዴ

አጥኚው ጥናቱን በሚያጠናበት ወቅት ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሐፍትን፣ ጥናታዊ ፅሁፎችን እንዲሁም መዛግብትና ምልከታ ላይ ተመስርቶ ጥናቱን አጥንቷል ፡፡ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን ይጠቀማል ፡፡ አለም እሸቱ << መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ>> በሚለው መፅሀፉ ስለ ገላጭ የምርምር ዘዴ የሚከተለውን አስፍሯል ፡፡

> ገላጭምርምር ገለፃን ትንታኔን እና አተረጓጎምን መሰረት
>
> የሚያደርግ ሲሆን በሁለትተለዋዋጮች መካከል
>
> የሚኖረውን ተዛምዶእያወዳደረና እያነፃፀረ ሊመለከት
>
> ይችላል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መረጃዎችንከተለያዩ
>
> ምንጮች የሚያሰባስብ ሲሆንትኩረቱን ግን የአንዱን
>
> ተጨባጭ ሁኔታትክክለኛ ባህሪ መግለፃፅ ወይም
>
> ማሳወቅይሆናል፡፡(1994፣148-149)

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተጠቀመው መረጃዎችን በገለፃና ማብራራት ላይ ትኩረቱን አድርጎ ስላጠና ነው ፡፡ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወለጋ ጃርደጋ ጃርቴ የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስረአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ባህሉ እንዴት እንደሚከናወን እና በትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን እንዴት እንደሚተነተን በገላጭ የምርምር ዘዴ በመጠቀም ጥናቱ ተጠንቷል ፡፡

### 1.6.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ የተለያዩ መንገዶች አሉ ። ያለው እንዳወቀ የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር በሚለው መፅሀፉ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እንደሚከተለው አስፍሯል ።

በምርምር ሂደት እንደ ምርምሩ አይነት እንደ ነጠኚዎቹ

ሁኔታ እንደ ተመራማሪው ችሎታ የገንዘብና የጊዜ መጠን ፣

የስልጠና እና የፍልስፍና ሁኔታ ለመረጃ መሰብሰቢያነት

የሚያገለግሉ በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አሉ ።

ዋና ዋና ዎቹ የሚከተሉት ናቸው ። 1. የፅሁፍ መጠይቅ

2. ቃለ መጠይቅ 3. ምልከታ 4. መዛግብት 5. የተለያዩ ፈተናዎች

6. ቡድን ተኮር ውይይት ። (2009 ፣ 147-148)

ይህ ጥንታዊ ፅሁፍ መዛግብት እና ምልከታን በመጠቀም በወለጋ የጃር ደጋ ጃርቴ የነቀተኒ የጋብቻ ስነስረአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር አጥንቷል ።

#### 1.6.1.1 መዛግብት

መዛግብት ጥናት ለሚያካሂድ አንድ አጥኚ ከጥናቱ ርዕስ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መፅሐፍ መፅሔት እና ጋዜጣ ጥናታዊ ፅሁፎች መረጃ ሊገኝባቸው የሚችሉ የሚነበቡ መዝገቦችን በመጠቀም መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው ። ያለው እንዳወቀ የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር በሚለው መፅሀፉ ስለ መዛግብት የሚከተለውን አስፍሯል ።

መዛግብት ተመራማሪው ስለ አለፈም ይሁን ስለ ወቅታዊ

ጉዳይ መረጃ ለማሰባሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ

ጠቃሚ ነገሮች ናቸው ። መዛግብት በፅሁፍ መልክ ከየቤተ መፅሀፍቱ

ቤተ መዛግብት ወይም ከሌሎች መሰባሰቢያ ቦታዎችና

እንደ ሁኔታውም ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች

ናቸው ፡፡ (2009 ፣ 191)

አጥኚው በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሀፍት እና ጥናታዊ ፅሁፎችን ስለሚቃኝ መዛግብትን ለመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተጠቅሟል ፡፡

## 1.6.1.2 ምልከታ

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን አገልግሎት ላይ አውሏል ፡፡ አለም እሸቱ መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ በሚለው መፅሀፉ ስለ ምልከታ የሚከተለውን አስፍሯል ፡፡

መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን

ትኩረት እና ምርምር የሚደረግ ምልከታ በአለፍ

አገደም አይተን የምናልፈው ጉዳይ ሳይሆን በቅድሚያ

ብዝመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት ነው ። (1994 ፣ 69)

አጥኚው ጥናቱን በሚያጠናበት የወለጋ ጃርደጋ ጃርቴ የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስረአት ላይ በምልከታ በሰበሰበው መረጃ ጥናቱን አጥንቷል ።

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በኦሮሚያ ክልል፣ሆሮጉድሩ ወለጋ ዞን፣በጃርደገ ጃርቴ ወረዳ በሚከናወነው የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስርአትን ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር ብቻ የሚተነትን ይሆናል፡፡

## 1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፋፈለ ነዉ።የመጀመሪያዉ ምዕራፍ መግቢያ ፣የጥናቱ ፣ዳራ ፣ የጥናቱ ንዑስ እና አብይ አላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ዘዴ፣የጥናቱ አደረጃጀት፣ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች እና የጥናቱ አነሳሽ ምክንያትን ይይዛል።ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ንድፍ ሀሳባዊ ቅኝት፣የትዉፊት ምንነት፣የትዉፊታዊ ተዉኔት መገለጫ ባህሪያት፣የትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን እና የተዛማች ጥናቶች ቅኝትን ያካተተ ክፍል ነዉ። ምዕራፍ ሦስት ዋናዉ የጥናቱ አካል ሲሆን በኦሮምያ ክልል በ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን የጀርደጋ ጀርቴ የጋብቻ ስነ ስርአት ከትዉፊትታዊ ተዉኔት አላባውያን አንፃር በሰፋት ይተነተንበታል። ምዕራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያ፣የመፍትሄ ሀሳብ፣ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ እና ዋቢ መፅሀፍት የሚቀርቡበት ክፍል ይሆናል።

# ምእራፍ ሁለት

## 2 ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የትዉፊት ምንነት

ትዉፊት የምንለዉ በአንድ ማህበረሰብ ዕምነት፣ ልማድና ባህል በማጠቃለል የአኗኗር ስርአታቸዉን በግልፅ የሚያስቀምጥ ካለፈዉ ትዉልድ ለሚመጣዉ ትዉልድ በቃል ወይንም በፅሁፍ የሚተላለፍ ነዉ። ትዉፊት ለብዙ ጊዜ በተወሰነ ማህበረሰብ የሚኖር ነገሮችን የሚተገብር መንገድ ነዉ።ትዉፊት አንድ ማህበረሰብ አምኖ የሚቀበለዉ የራሱ የሆነ ህግና ደንብ ያለው ማህበረሰቡ ሊተዳደርበት የሚችል ነው። ፍቃደ አዘዘ ስለ ትውፊት ምንነት ''ትውፊት ምንድነው? ትውፊት በስነ-ፅሁፍ ውስጥ'' በተሰኘው መፀሀፉ እንደሚከተለው አስፍሮታል ።

> "ትውፊት የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር የምያደርገውን እና የተደረገውን ትግል ከቦታ፣ከሀገር ሀገር ያደረጋቸውን ጉዞዎች፣በትናንሽ እና በትላልቅ ግዛቶች መካከል የነበረውን ጦርነቶች፣በውሀና እና በግጦሽ ግጭቶች የመኖር ሚስጥር የሕይወት እና የሞት ትርጉም ለማግኘት ያደረገውን ጥረት ይዞ ይገኛል።ትው-ፊት በወንዶች እና በሴቶች፣በሰዎች እና በእንሳት መካከል የነበረውንና ያለውን ግንኙነትአካቶ የያዘ እና የተሰጠውን የተመለከተበት፣ነገውን ያውጠነጠነበት፣ ዛሬውን ያተኮረበት፣የብዙ ዘመን እውቀት እና ልማዱን ያመቀበት ትውፊት ነው"(1976:24)

ትውፊት አያት ተቀብሎ ላባት አባት ለልጅ ልጅም ለልጅልጅ እያለ ከላይሲወርድ ሲዋረድ ማህበረሱቡ ማንነቴ መለያዬ ነው ብሎ ከውስጡ አስቀምጦ የሚተገብረው ማህበራዊ ተግባር ነው:: ትውፊት እንደ ማህበረሰቡ አቀባበል እየደመቀም ሆነ እየደበዘዘ ይመጣል:: አንድ የሆነ ማህበረሰብ የራሱን ትውፊት ችላ እያለው በሄደ ቁጥር አብሮ እየደበዘዘ እንደሚሄደው ማህበረሰቡ ቦታ ሰጥቶ ሲተገብረውም ትውፊቱ እየሰፋና ስር እየሰደደ ቀጣይነቱ ለትውልድ ይፋ ይሆናል።

## 2.1.1 የትዉፊታዊ ተዉኔት ምንነት

ትውፊታዊ ተውኔት የማህበረሰብ ባህል፣ እምነት መሰረት አድርጎ የሚሰራ ወይም የሚከናወን የተውኔት አይነት ነዉ፡፡ትዉፊታዊ ተዉኔት የድራማ፣የዘፈን ፣እና የዉዝዋዜ ጥምረት ሲሆን አንድ ማህበረሰብ ከሌላዉ ማህበረሰብ የሚለይ እና በቦታና እና በጊዜ የተገደበ ነዉ፡፡ ፋንታሁን እንግዳ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸውከ ሀ እስከ ፐ በተሰኘው መፅሀፉ ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የሚከተለውን አስፍሯል ፡፡

**ከህዝባዊ ልማዶች እምነቶች ክብር በአሉች እና ስነ-ቃሎች**

**ላይ ተመስርቶ የሚመደረክ ባህላዊ ትርኢት ነው፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት**

**በፅሁፍ የሚቀመጥ ጽሁፍ ተውኔት የለውምከትውልድ ወደ ትውልድ**

**በቃል እየተላለፈተሰሚነት ይቀርባል፡፡**(1993 ፣57)

ትውፊታዊ ተዉኔት የማህበረሰቡን ኑሮ ከ ግዜ ወደ ግዜ ተግባራዊ በሆነ መንገድ የሚገልፅ ነዉ፡፡ ስለ ትውፊት ሲነሳ "folklore" ማንሳታችን አይቀሬ ነው፡፡folklore ’folk’ እና ’lore’ ከተሰኙ ሁለት ቃላቶች የመጣ ሲሆን "folk" ማለት ህዝብ ማለት ሲሆን lore ደግሞ የኣንድ ማህበረሰብ ባህል ወይም ታሪክ ማለት እንደሆነ ሊቆች ይናገራሉ፡፡ ስለዚህም folklore በዉሰጡ ሰፋ ያለ ፅንሰ ሃሳብን የያዘ ነዉ፡፡ ልክ እንደ ፎክ ዘፈን፣ፎክ ዉዝዋዜ፣ፎክ ተረት፣ፎክ እምነት እና ሌሎቹንም በዉሰጡ ያጠቃልላል፡፡ባህል የተለያየ እንደ መሆኑ መጠን በጥበቡ ኣለም ማለትም በቴአትር የተለያዩ ኣይነት ባህሎችን ሳይከለስ እና ሳይበረዝ ባህሉ እንደተጠበቀ ወደ ቃለ ተዉኔት በመለወጥ የባህሉን  ምንነት እና እንዴት በመድረክ ላይ በመመድረክ ማሳየት የትዉፊታዊ ተዉኔት ኣንዱ ገፅታ ነዉ፡፡ትዉፊታዊ ተዉኔት ብዙዉን ግዜ የምንፅፈዉ እየፈጣርን ኣይደለም፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት የኣንድን ህብረተሰብ እሴት በተጠበቀ መልኩ ያለዉን እንዳለ ወደ መድረክ የመቀየር ጥበብ ነዉ፡፡

## 2.1.2 የትዉፊታዊ ተዉኔት መገለጫ ባህሪያት

ትዉፊታዊ ተውኔት እንደሌሎቹ የቴአትር ዘዉጎች ማለትም ታሪካዊ ተውኔት፣ሀይማኖታዊ ተውኔት፣አፈ-ታሪካዊ ተውኔት እና ምናባዊ ተውኔት የራሱ የሆነ

መገለጫ ባህሪያቶች ይኖሩታል። ትውፊታዊ ተውኔት ከዘልማዳዊ ተውኔት የሚጋራቸው እና የሚለይባቸው ይዘቶች እና ነጥቦች አሉት።ይህን በተመለከተም ፋንታሁን እንግዳ << ተዉኔታዊ መዝገበ ቃለትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ-ፐ >> በሚለዉ መፅሃፉ የሚከተለዉን ይገልፃል፦

> የትዉፊታዊ ተዉኔት ስርአት ከሌሎች ተዉኔት የሚለየዉ
>
> ሙሉ ለሙሉ አለማዊ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት
>
> ስለማያደርግ ነዉ።ትዉፊታዊ ተዉኔት ትርኢት በማህበራዊ
>
> ኩነታዎች ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን ኣልፎ ኣልፎ ህፀያችን
>
> ወይም እንከኖቹን በማሽሟጠጥ ላይ ያተኩራል።(1983፣53)

ከላይ ከቀረበዉ ገለፃ የምንረዳዉ ትዉፊታዊ ተዉኔት ከሌሎች የተውኔት ዘዉጎች ከሚለይባቸው መገለጫዎች መካከል በኣንድ ማህበረሰብ ክዋኔዎች ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ እንዲሁም ህፀያቹን ወይም እንከኖቹን በማሽሟጠጥ እንደሚያቀርብ እንረዳለን። በተጨማሪም ፋንታሁን እንግዳ ከላይ በተገለፀ መፅሃፋቸዉ ትዉፊታዊ ተዉኔት ከሌሎች ዘዉጎች ሲነፃፀር መለያ ባህሪያቱ እንደሚከተለዉ ኣቅርበዋል፦

1. የትዉፊታዊ ተዉኔት ተመልካች እራሱን የትርኢት ኣካል ኣድርጎ በመቁጠር በንቃት ይሳተፋል።

ይህም ማለት የሚመደረከው ትውፊታዊ ተውኔት የማህበረሰቡን የባህል አኗኗር እና የዕለት ተዕለት የወግ እና ልማድ ኩነቶች በመሆኑ ተመልካች እራሱን የተውኔቱ ትርኢት ውስጥ በማስገባት የእኔ ታሪክ ነው ብሎ ይከታተላል።በመሆኑም የሚመደረከው ትውፊታዊ ተውኔት በአቀራረቡ ለተመልካች ቅርብ በመሆኑ ተመልካች እራሱን የትርኢቱ አካል በማድረግ በነቂስ ይሳተፋል።

2. የትዉፊታዊ ተዉኔት ትርኢት የሚቀርብበት በደንበኛ ቤተ ተዉኔት ሳይሆን በገላጣ ስፍራ ነዉ።

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ትውፊታዊ ክንዋኔዎችን ማህበረሰቡ የሚከወኑት በተራራ ስፍራ፣ሀይማኖታዊ ስፍራ፣በዛፎች ስር፣ወንዞች አከባቢ እና በመሳሰሉት ስፍራዎች ነው፡፡የሚቀርበው ትውፊታዊ ተውኔትም የትውፊታዊ ተውኔት ድባቡን ለማምጣት እና የተመልካችን እንዲሁም የትውፊቱ ባለቤት በሆነው ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ነው፡፡በተጨማሪም ተውኔቱ ለትውፊቱ ቅርብ ሆኖ ተአማኒነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡እንዲህ በመሆኑም ተመልካች የክዋኔው አካል በመሆን ተውኔቱን ይመለከታል፡፡

3. የትዉፊታዊ ተዉኔት በመዝሙርና በዉዝዋዜ ይታጀባል፡፡

አብዛኛው የተለያዩ ማሕበረሰብ ትውፊት ለክዋኔያቸው ማጀብያ (ለስረአቱ ድምቀት) በዘፈን እና በጭፈራ ወይም በውዝዋዜ ይታጀባል፡፡ክዋኔው ላይ የሚታደም ታዳሚም በዚህ በመዝሙር እና በጭፈራ ክዋኔውን ያጅባል፡፡በዚህም መሰረት ትውፊታዊ ተውኔት ከማህበረሰቡ (ከትውፊቱ ባለቤት) በቀዳው ዜማ እና ውዝዋዜ ታጅቦ ይቀርባል፡፡

*4. የትዉፊታዊ ተዉኔት ገፀ ባህሪያት ሁሉም አስተኔ ናቸዉ፡፡*

እንደሚታወቀው በአንድ ትውፊታዊ ክንውን ውስጥ የተለያየ አይነት የሚና ክፍፍል ይኖራል፡፡ይህም አንድ ሰው ሙሉ ለሙሉ ትውፊቱን ብቻውን ሊያከናውን የሚችል አይሆንም፡፡ምክንያቱም ትውፊት የግለሰብ ሳይሆን የማሕበረሰብ ነውና፡፡በመሆኑም በዚህ የሚና ክፍፍል ውስጥ ትውፊቱን ለመከወነ እንደየ እድሜው እና ትውፊቱ ላይ ባለው ደረጃ (እርከን) የስራ ድርሻውን ይወጣል፡፡ትውፊቱ ወደ ተውኔት ሲቀየርም ሁሉንም የትውፊቱን የስራ ድርሻ ወይም ድርጊት አንድ ገፀ-ባህርይ ብቻ የሚጫወተው ባለመሆኑ እና በተውኔቱ መሀል ላይ ሊወጣ ወይም ሊገባ ስለሚችል ገፀ-ባህርዮች አስተኔ ናቸው፡፡ትውፊቱን አስጀምሮ በዛው የሚወጣ ገፀ-ባህርይ ሊኖር ይችላል፤እንዲሁም የትውፊቱ ማሳረጊያ ላይ የሚገባም ገፀ-ባህርይ ሊኖር *ይችላል፡፡በአጠቃላይ በአንድ ትውፊታዊ ክንውን ውስጥ ታሪኩን ብቻውን ተሸክሞ የሚጓዝ ገፀ-ባህርይ አይኖርም፡፡*

5. በትዉፊታዊ ተዉኔት ጥቅም ላይ የሚዉሉት የመድረክ ቁሳቁሶች፣ባህላዊ ከበሮች ጭንብሎችና የመሳሳሉት ናቸዉ፡፡

ይህ ማለት ትውፊት እንደሚታወቀው ከአለፈው (ከቀድሞ) ትውልድ ሲወርስ ሲዋረስ የመጣ ስረአት እንደመሆኑ ባህላዊ የሆኑ ቁሳቁሶች በመድረክ ላይ ይስተዋላሉ፡፡ለምሳሌ ትውፊት

በመዝሙር የሚታጀብ እንደመሆኑ መጠን መዝሙሩን ለማድመቅ ከበሮ ያስፈልጋል።ስለዚህ ከበሮ እንደ አንድ ቁስ በመድረክ ላይ ይታያል።እንዲሁም ትውፊቱ ላይ የተለያየ አይነት ገፀ-ባህርይ ስለሚኖር ገፀ-ባህርዩውን ለመምሰል የተለያዩ የፊት ጭምብል ይጠቀማል።በተጨማሪም ትውፊታዊ ተውኔቶች በገላጣ ስፍራ በመቅረባቸው በጥንት ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ ለማድረግ እና ተመልካች ጋር በተገቢው ሁኔታ እንዲደርስ ጭምብልን እንደ ድምፅ ማጉያ ሲጠቀሙ ነበረ።ስለዚህም ከበሮ እና ጭምብልን ጨምሮ ሌሎች ትውፊቱን የሚወክሉ ቁሶች በመድረክ ላይ ሊታዩ ይችላሉ።

6. ከዚህ በተጨማሪ ትዉፊታዊ ተውኔት ቁርጥራጭ ትዕይነቶችን የሚያገናኝ ተራኪ ይጠቀማል።

በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የትውፊቱን አንድ አንድ ድርጊቶች ወደ መድረክ ለማምጣት ይከብዳሉ፤ለዚህም ድርጊቱ በትረካ ይገለፅ ዘንድ ተራኪ ያስፈልጋል።እንዲሁም ከአንድ ትዕይንት ወደ ሌላ ትዕይንት መሸጋገርያ እና ቁርጥራጭ ትዕይንቶችን በማገናኘት ትዕይንቶቹ ትርጉም ያላቸው እና መልዕክታቸው እንዳይዛባም ተራኪ በሚያስፈልግቀት ቦታ በየመሀሉ እየገባ ሊተርክ ይገባል።

## 2.2 የትዉፊታዊ ተዉኔት ኣለባዉያን

### 2.2.1 ቃለ ተዉኔት

የሰዉ ልጅ በማህበረሰብ ዉስጥ መግባባት ይኖረዉ ዘንድ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ንግግር ይኖራል። ሰዎች በእለት ተለት ክዋኔያቸዉ ዉስጥ በቃለ-ምልልስ ወይም በንግግር ይግባባሉ። ንግግርን (ቃለ-ምልልስን) ወደ ትዉፊታዊ ተዉኔት ኣምጥተን ስንመለከት በትዉፊታዊ ተዉኔት ዉስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ኣለዉ። ይህም ጠቀሜታዉ በተለያየ ደረጃ ይገለፃል።ለምሳሌ የትዉፊታዊ ተዉኔት ቃለ ተዉኔት የገፀ ባህሪዉን ስብዕና፣የገፀ-ባህሪያትን ማንነት ብሎም የገፀ- ባህሪያትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚገልፅ ነው።ቃለ ተዉኔት እንደ ሌሎች የተዉኔት ኣይነቶች ሳይንሳዊ ሳይሆን በተለምዶ በማህበረሰቡ መካከል የሚደረግ ንግግርን መሠረት ያደረገ ነዉ።

ቃለ ተዉኔት የተመረጠና የገሀዱን ኣለም ሰዉ ማንነት የሚገልፅ ነዉ።በመሆኑም በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥም የገፀባህርይውን ሚና፣የኑሮ ደረጃ እና የመሳሰለውን በመግለፅ ረገድ ትልቅ ሚና አለው። ሆኖም ቃለ-ተውኔት እና የተሳሉት ገፀ-ባህርያት መመጣጠን

አለባቸው::ይህንንም ፋንታሁን እንግዳ 'የተውኔት አፃፃፍ ዘዴ' በተሰኘው መፀሀፉ እንዲህ ሲል ተንትኗል፦

> ቃለ-ተውኔት ለተሳለው ገፀ-ባህሪ ተገቢ እና ተፈጥሯዊ መሆን አለበት::ይህም ሲባል ገፀባህሪው የንግግር ተፈጥሮውን ምን እንደሚመስል እና በምን ምክንያት አሁን የነበረውን ንግግር ልይዝ እንደቻለ መጠየቃችን አይቀርም::ተገቢ መልስ የምናገኘው ታድያ የገፀ-ባሕርያቱን የአሳሳል ደረጃዎችን መለስ ብለን በማጤን የገፀ-ባህርያትን ቃላዊ አቋም፣አካላዊ አቋም፣ማሕበራዊ ግንኙነት፣ስነ-ልቦናዊ እና ተፈጥሮን ጠንቅቀን ካወቅን ብቻ ነው::(1992:47)

ይህ ማለት አንድ በተውኔት ውስጥ በክፋት የተሳለው ገፀ ባህርይ የክፋቱን መጠን ሊገልፅለት በሚችል መልኩ ቃለ-ተውኔት ሊዘጋጅለት ይገባል::አለበለዝያ የሚፃፈው ተውኔት ከገሀዱ አለም ሊርቅ ይችላል::እንዲሁም ንግግሩን የሚናገረው ገፀ ባህርይም በምን ምክንያት እንደዛ መናገር እንደቻለ እና ለምን በንግግር ወቅት እነዛን ቃላት እንደተጠቀመ ተገቢውን ምክንያት ሊቀመጥ ይገባል::በዚህም መሰረት ቃለ-ተውኔት የአንድን ገፀ-ባህርይ ማንነት በመግለፅ ረገድ የጎላ ሚና አለው::

### 2.2.2 መቼት

መከወኛ ቦታ (መቼት) ማለት አንድ ተዉኔት ተጀምሮ እስኪያልቅ የሚከወንበት ቦታ ነዉ:: መቼት የ ሶስት(3) ነገሮች ጥምረት ነዉ:: እነሱም ግዜ፣ቦታ፣እና ማህበራዊ ሁኔታ ናቸው:: የትዉፊታዊ ተዉኔት መከወኛ ቦታዎች ከማህበረሰቡ እምነት ጋር ተዛማጅ ሆነዉ እናገኛቸዋለን:: ይህም የማህበረሰቡን የኣኗኗር ስርዓት ኣጉልቶ ከማሳየት አኳያ የጎላ ሚና ኣለዉ::በብዛት በትዉፊታዊ ተዉኔት ዉስጥ መከወኛ ቦታ ሲሆኑ የሚስተዋሉት ቦታዎች ወይም መከወኛ ቦታዎች በተራራማ ቦታ፣በወንዝ ዳር፣በእምነት ቦታዎች ላይ እና በመሰሳሉት ስፍራዎች ነው::ይህም ከማህበረሰቡ የኣኗኗር ሁኔታ ጋር ቁርኝት ኣለዉ::

እነዚ የመከወኛ ቦታዎችም ኣንዳኣንድ ግዜ ከሰርዓተ ሃይማኖት ክዋኔ ጋር የሚመሣሠሉበት ግዜ ኣለ::እንዲሁም መቼት ከጊዜ እና ቦታ ባሻገር ከገፀባህርያቱ ጋር የተያያዘ ተፈጥሯዊ የመልከአምድር አቀማመጥ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ ቦታዎችን ያካትታል::ይህንን አስመልክቶ ዘሪሁን አስፋው 'የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን' በሚል መፀሀፉ እንዲህ ገልፆታል ::

"መቼት ታሪኩ የተከናወነበት እና ገፀ-ባህርያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት የገጠር ወይም የከተማ አከባቢ ብቻም አይደለም፥አያሌ ነገሮችን ይጨምራል።ከገጠሩ እና ከከተማው ሕይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አካቶ በመያዙም ጓዘ ብዙ ነው።"(2005:179)

## 2.2.3 የሚና ክፍፍል

በትዉፊታዊ ተዉኔት የሚና ክፍፍል ከዋኙ ከትዉፊቱ ባለቤት ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር ያለዉ ቀረቤታና ትዉፊቱን የሚያዉቀበት መጠንን መሠረት አድርጎ ዕድሜን፣ፆታን፣ብሎም የእዉቀት መሰረት ኣድርጎ የሚሰጥ ነዉ። በመሆኑም ይህን መሰረት ኣድርጎ የተሰጠዉ ከዋኝ ስራዉ በደስተና በፍቅር መወጣት ይችላል። **ፋንታሁን እንግዳ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ‹‹ሀ››እስከ ‹‹ፐ›› በተሰኘው መፅሀፍ ስለሚና ክፍፍል እንደሚከተለው አስፍሯል።**

> **ተዋንያን የሚጫወቱበት ድርሻ ነው። የሰው ልጅ በእለታዊ ህይወት የሚወጣውሚና እና ተዋናይ በመድረክ ላይ የሚተውኑት ሚና ተብሎ በሁለት አብይ ክፍል ሊካፈልይችላል። በአጠቃላይ የመድረክየትወናሚናታስቦበት ተጠንቶ ለመቅረቡ ተዋንያኑም ተመልካቹም የሚረዱ ጉዳይ ሲሆን የማህበረሰባዊና ግለሰባዊ ሚናዎች በእያንዳንዱግለሰብየመድረክ ወይም የመቀፀል ችሎትየሚወሰን ይሆናል።** (1993፣29)

የትውፊታዊ ተውኔት ሚና ክፍፍል ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት ኑሮ በእድሜ በፆታ ሃላፊነትን ወስደው የሚከውኑትን ክዋኔ ነው። ይህም ማለት እንደ ማህበረሰቡ ባህል አባት ይሄን ይሰራል፣ልጅ ይሄን ያደርጋል፣ሴት ይሄን ታደርጋለች፣ወንድ ይሄን ይከውናል ተብሎ በማህበረሰቡ የተለመደ ልማድን መተግበር ነው። በአጠቃላይ የመድረክ የትወና ሚና ታስቦበት ተጠንቶ

ለመቅረቡ ተዋንያንም፣ተመልከቹም የሚረዱት ጉዳይ ሲሆን፣ማህበራዊና ግለሰባዊ ሚናዎች በእያንዳንዱ ግለሰብ የመቀፀል ችሎታ የሚወሰን ይሆናል። ሚና ክፍፍል በትውፊታዊ ተዉኔት የጋራ ስራ ነዉ። የተሳታፊዎች ሚና የሚገለፀዉ በተግባራቸው(ድርጊታቸው) እና ቃለ ምልልስ ነዉ።

## 2.2.4 ቁሳቁስ

በክንውን ወቅት ሰዎች የሚጠቀሙበት ማንኛውም አይነት መገልገያ የሆኑ ቁስ ያጠቃልላል። አብዛኛውን ጊዜ የሰው ልጅ የዕለት ዕለት እንቅስቃሴያቸው ወቅት የሚገለገልበት መሰረታዊ ረዳቶች ናቸው።ፈንታሁን እንግዳ፣ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ- ፐ>> በሚለው መፅሃፉ ስለ ቁሳቁስ የሚከተለውን አስፍሯል ።

"ቁሳቁስ አራት ክፍሎች አሉት።አንደኛው የመድረክ ቁሳቁስ የሚባሉት
ተዋንያን በመድረክ ላይ በእጃቸው የሚይዟቸው እንደ ደብዳቤ፣ብርጭቆ፣
ሳህን የመሳሰሉት ናቸው።የመድረክ የትዕይንቱ አካል ሆነው የሚቀርቡ
መቀመጫ፣ወንበሮች፣አልጋ፣ቁምሳጥን፣የውሀ ማቀዘቀዣ የመሳሰሉት ናቸው።
ከዚህ በኂላ የግድግዳ ጌጣጌጦች ለምሳሌ እንደ የሚለጠፉ ስዕሎች፣
የመስኮት መጋረጃዎች፣የግድግዳ መስታወቶች እና የመሳሰሉት ናቸው። (1993 :85)

ቁሳቁስ ማንኛውም አይነት ቁስ ሆኖ ለዬትኛውም ክዋኔ የተለየ ጥቅምን የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። የሰው ልጅ ሲንቀሳቀስ ወይም ሲቀመጥ ቁሳቁስን ይጠቅማል።

## 2.2.5 አልባሳት

አልባሳት የሰው ልጆችን ማንነት ይገልጽልናል፤ማለትም የአኗኗሩን ሁኔታ የስራ ድርሻውን የመሳሰሉትን ይገልጻል።ወደ ትወናም ሰንመጣ ማህበራዊ ሁኔታውነ ግልጽ አድርጎ ያስረዳናል።ፋንታሁን እንግዳ 'ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ' በሚል መፀሀፉ አልባስን አስመልክቶ እንደሚከተለው ገልፆታል፦

"አልባሳት ተዋንያን ዝግጅታቸውን በመድረክ ለህዝብ በምያቀርቡበት

ጊዜ የሚለብሱት ልብስ መጠሪያ ነው፡፡አልባሳት የሚለው ቃል የመጣው ወይም ምንጩ ከቤተ-ክርስትያን ነው፡፡ቀሳውስት፣ጳጳሳት እና ዲያቆናት በክብረ-በዓላት እንዲሁም ለስረአተ-ቅዳሴ ወደ ቤተመቅደስ በሚገቡ ጊዜ የሚ ለብሱትን ልብስ እና የሚዘረጉትን ጃንጥላ ይጨምራል፡፡አልባሳት ጊዜን ቦታን፣የኑሮ ጀረጃን፣እምነትን፣ፆታን፣የሙያ መስክን፣ግላዊ ፀባይን እና የን ቃተ-ህሊናን ደረጃ ሳይቀር ሊወክሉ ወይምሊጠቁሙይችላሉ፡፡"(1993:62)

አልባሳት የገጸ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃ /ሁኔታ/ ይገልጻል፤በገፀባህሪያት መካከል የተለያዩ የሚና ክፍልልን ለመፍጠር እንዲሁም እነዚህን አልባሳት ለተለያዩ ጠቀሜታዎች ይውላል፡፡ አልባሳት ጊዜን፣ቦታን፣የኑሮ ሁኔታን፣ጾታን እና ማህበራዊ እውነታን ይገልፅልናል፡፡ አልባሳት ትውፊታዊ ተዉኔት በሚከወንበት ጊዜ ከዋኞች እና ተሳታፊዎች የሚለብሱት ልብስ ሲሆን ከዋኞች በሚከውኑት ሚና ልክ ባህልን፤ወግን ፤ህይማኖትን እንዲገልጽ ተደርጎ እንዲለብሱ ይደረጋሉ

## 2.2.6 ከዋኞች

ከዋኝ የምንለው ሰዎችን ሲሆን ድርጊት ደግሞ የሚፈጸመው ተፈጻሚ አካል ነው፡፡ ሆኖም ድርጊት በጥበብ ዕይታ ሲታይ በመድረክ ላይ ተዋናይ ገጸ ባህሪውን ተላብሶ ሚናውን በሚያሳይበት ወቅት የተለያዩ ድርጊቶች ያሳያሉ፡፡

በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ሰዎች የዕለት ዕለት ህይዎትን ሲኖሩ በማወቅም ሆነ ባላማወቅ የተለያዩ የሚያስቱና የሚያስከፉ ድርጊቶችን ሊፈጽም ይችላል፡፡ በተለይ ትወፊት ከባህል ጋር ሲያያዝ ሰዎች አምነው የሚገዙበት የራሳቸው የሆነ ባህልና ዕምነት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ባህሉ የሚፈቅደውን ማህበረሰቡ የሚያምንበትን የተለያዩ ድርጊቶች ይፈጸማሉ፡፡ ከዋኞችም ለድርጊቱ አስፈላጊ ነገሮችን በመጠቀም የአንድን ማህበረሰብ ባህል ትውፊታዊ ይዘቱን መድረክ ላይ ያሳያሉ፡፡

## 2.2.7 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት

አጥኚው ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሰራ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች ለማየት ሞክሯል።አጥኚው በቀጥታ ከስረአቱ ጋር የተገናኘ ጥናታዊ ፅሁፍ ባያጋጥመውም የተለያዩ ስረአቶች ከ ትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር የተሰሩትን ማየት ችሏል።በዚህም መሰረት በ 2013 ዓ/ም ዮሀንስ አበራ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለ ባችለር ኦፍ አርትስ ድግሪ ማሟያነት የሰራው "የአቴቴ ሲንቄ ክዋኔ ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር" የተሰኘውን ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው ለመዳሰስ ሞክሯል።

የዮሀንስ አበራን እና ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያመሳስላቸው ነገር ሁለቱም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ ስረአቶች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ናቸው።ሌላኛው የሚያመሳስላቸው ነገር ሁለቱም ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ነው የተጠኑት።ሁለቱም ጥናቶች አራት አራት ምዕራፎችን የያዙ ናቸው።ሁለቱም ጥናቶች የተጠኑበት የጥናት ዘዴ እና ቅርፅ ያመሳስላቸዋል።

ሁለቱን ጥናቶች የሚያለያያቸው ነገር ደግሞ የዮሀንስ አበራ ጥናት ርዕስ "የአቴቴ ሲንቄ ክዋኔ ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ሲሆን የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ መጠርያ ርዕስ ደግሞ "የነቀተኒ የጋብቻ ስነ -ስረአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር" ይሰኛል።በዚህም መሰረት ሁለቱ ጥናቶች በርዕሰ ይለያያሉ።ሌላ የሚያለያያቸው ጉዳይ የዮሀንስ አበራ ጥናታዊ ፅሁፍ በኦሮሚያ አርሲ ዞን በሚኖሩ ማህበረሰብ ላይ ሲሆን ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን በኦሮሚያ ክልል ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ነው።በመሆኑም ሁለቱ ጥናቶች በተለያየ አከባቢ በሚኖሩ ማህበረሰቦች ላይ በመሰራታቸው በቦታ ይለያያሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. መረጃ ትንተና

### 3.1. የነቀተኒ ምንነት

የጋብቻ ዋና አላማ የሰው ልጅ ከብቸኝነት ህይወት የሚላቀቅበት ከፈጣሪ የተሰጠ ፀጋ ነው።የሰው ልጅ ጋብቻን በተለያዩ መንገዶች ይፈፅማል። የኦሮሞ ብሔረሰብም ልጆቻቸውን ትዳር ለማስመስረት የተለያዩ ባህላዊ መንገዶችን ይጠቀማል። ከዚህም መካከል በኦሮሚያ ክልል፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን፣ በጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ የሚከናወነው የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርዓት አንዱ ነው።

ነቀተኒ በ አማረኛ አቻ ፍቺ ባይኖረውም ‹‹ልመና›› ወደ ሚለው የአማረኛ ቃል ይጠጋል። ነቀተኒ አንድ ወጣት ዕድሜው ለጋብቻ ሲደርስ የልጁ አባት ልጁን በትዳር ለማጣመር ለልጁ የትዳር አጋር የሚፈልግለት ስነስርዓት ነው። በዚህ የነቀተኒ ጋብቻ ስነስርዓት ላይ አባት ለወንድ ልጁ የምትሆነውን የትዳር አጋር ሴት ሲፈልግለት ልጅቷን በማየት ሳይሆን የልጅቷን ቤተሰብ ማንነት በማየት እና በማጥናት ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ አንድ አባባል አለ። እሱም "Haadha Ilaalani Intala Fudhu"(እናቷን አይተው ልጅቷን ያገባሉ) እንደማለት ነው። የዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ የሚያምንበት አንድ ባህል አለ። እናቷ ጎበዝ እና ባለሞያ ከሆነች ልጅትም እንደ እናቷ ጎበዝ እና ባለሞያ ትሆናለች ብለው ያስባሉ። በዚህም ምክንያት ነው ከልጅቷ ይልቅ ቤተሰቧን የሚያጠኑት። አባት ስለ ልጅቷ ቤተሰብ በደንብ ካጠና በኋላ ከቤተሰቦቹ ጋር ዝምድና ከሌለው እና ቤተሰቦቹን ከወደደ የጋብቻ ደብዳቤ ለልጅቷ ቤተሰብ ይልካል።

የልጅት ቤተሰብም ደብዳቤውን በመቀበል ካነበቡ በኋላ ደብዳቤ ስለላከው ቤተሰብ ጥናት በማድረግ በዘር፣ በሀብት እና በመሳሰሉት ነገሮች የሚመጣጠኑ ከሆነ እሺታቸውን ይገልፃሉ። በዚህ መንገድ በሁለቱ ቤተሰብ መሀል የሚከናወነው የሰርግ ስነ-ስርዓት ነቃተኒ በመባል ይታወቃል።

## 3.2 የነቀተኒ የሰርግ ስነ-ስርዓት ከትውፊታዊ ተውኔት አለባውያን አንፃር

### 3.2.3 ከቃለ- ተውኔት አንፃር

በነቃተኒ የጋብቻ ስነስርዓት እንደ ቃለ-ተውኔት ወይም ንግግር የሚወሰደው ምርቃት፣ ዘፈኖች እና ተማፅኖ ነው፡፡ አባት ደብዳቤ ልኮ ከተመለሰለት በኂላ ሽማግሌዎችን ሲሰበሰብ እንዲህ በማለት ይናገራል፡፡

1 Abba:- bayyachufaan jeedha sif ha millka'uu nan jeedha.

Jarsa:- sif ha millka'uu bayyadhuu

Abba:- Ulfiaachuufan jedha Ulfadhuu nan jeedha

Jarsa:- Ulfataadha duraanu Ulfaatdhu

Abba:- Wanan isiin bira dhufeef beektanituu gammachuun koo akka gammachuu keessanitii naf lakkoftaanii Ulfinaa gammachukoof akka akka deebii naf kenitanifaan dhufee

Jarsaa:- garii gotee gammachuunke gammachuu keenya. Baga nagaan dhuftee. Hintala eenyuu barbaadde?

1 አባት፣ ልበዛ ነው ያርግልህ ባሉኝ!

ሽማግሌ ፡- አዎ ያርግልህ ---ብዛ

አባት፡- ልከበር ነው ክበር በሉኝ!

ሽማግሌ፡- ክቡር ነህና ክብር ልበስ

አባት፡- የመጣውበትን አውቀዋልና ደስታዬን እንደ ደስታችሁ በመቁጠር የደስታን ካባ እንድታለብሷኝ ፈልግያችሁ መጣው

ሽማግሌ፡- መልካም አደረግክ ደስታህ ደስታችን ነው፡፡ እንኳንም መጣህ፡፡ ለመሆኑ ልጅት የማናት?

.

እያሉ ካለልጅቱ ቤተሰብ ይወያያሉ፡፡ አባት ሁሉም ሽማግሌዎች ጋር ሲሄድ ተመሳሳይ ንግግር ካደረገ በኋላ ሽምግልና የሚሄዱበትን ቀን ተቀጣጥረው ይለያያሉ፡፡ ሽማግሌዎችም ወደ ልጅት ቤተሰብ ሲሄዱ ውጪ ቆመው ከእናትና አባት ጋር ይነጋገራሉ፡፡

2 Abba hintaala:-Baga nagaan dhuftaan seena
Jarsaa 1:-Baga nu ulfeesitaan ulfaadha garuu har'a seenuf hin dhufnee.
Jardaa 2:- lapheen kenyii ala turu jalaateera.
Jarsaa 3:-Amma lapheen keenya ol seenu filatuutii bakkee kana ha teenyuu

2 አባት ፡- እንኳን መጣችሁ ግቡ

ሽማግሌ 1፡- እንኳን አከበረችሁን ክብሩ!ግን ዛሬ መግብያችን አይደለም

ሽማግሌ 2፡- ልባችን ከውጪ ያቀመጥ ዘንዳ ወዷል፡፡

ሽማግሌ 3፡- ልባችን ለቤት ውስጥ መቀመጥ እስኪፈቅድ

ከዚህ ከደጃፍ እናውጋ

(እናት ውጪ የሚቀመጡበትን ቦታ ታሰናዳና ውጪ ይቀመጣሉ)

3 Abba hintalaa:- noora
Jarsaa 1:- dubiin nu'i itii garakee dhufnee duresee si ga'eera Abban ''eebelu'' gammachuusa siniin ga'u filateera kanaf mana ketii argaamne
Abba hintala:- Gammachichi ananis dabalateetii.

3 አባት፡- አረፍ በሉ

ሽማግሌ 1፡- ነገሩ ከጆሮዎት ደርሷልና 'የእከሌ' አባትም ደስታውን እንካፈል ዘንዳ ስለወደዱ እርሶ ቤት ተገኘን፡፡ የእርሶም ደስታ ከሆነ በጋራ ልናወጋ እና ስለ ስርጉ አካሄድ ለመታዘብ መጥተናል፡፡

አባት፡- እንዴታ ደስታው የእኔም ጭምር ነው፡፡ (በማለት እሺታቸውን ፈቅደው ስለ ሰርጉ ይወያያሉ)

ሌላው በነቀተኒ ሰርግ ላይ እንደ ቃለ-ተውኔት የሚታየው በተለያየ ቦታ የሚዜሙ ዜማዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ልጁ ወዷት ልጅት ግን ዕድሜዋ ለጋብቻ ሳይደርስ ሲቀር እና ፍቃደኛ ሳትሆን ቀርታ በግድ ሲድሯት እንደ ሚከተለው የውስጧን ስሜት በዜማ ትገልፃለች፡፡

4 *Harmii koo hin baane*

*Ni quuquxe malee*

*Ya haayyooleekoo*

*Laanni koo hin geenye*

*Naquuftani malee*

4 ጡቴም አላደገ ጉች ጉች አለ እንጂ

እናቶቼ ሆይ ጋብቻዬስ አልደረሰም ሰለቻችሁኝ እንጂ

በዚህ መልኩ ልጅቷ ለጋብቻው ፍላጎት ከሌላት በዜማ ስሜቷን ታንጎራጉራለች፡፡ እንዲሁም ሰርጉ ከመድረሱ በፊት አስቀድመው በሙሽሪት ቤት በሚጨፈረው ጭፍራ ላይ የሙሽሪት ቤተሰቦች እንዲህ በማለት ሙሽራውን ይሰድቡታል፡፡

5 *Yaa hiddi koololee jimmaa*

*Yaa gurbaa osolee ilmaa*

*Haatii kee duutemoo jirti*

*Gurgureetu okkotee binna*

5 የምታምር እምቧይ ሆይ

አንተ ልጅ ሆይ

እናትህ ከወዬት አለች

ሸጠናት ማሰሮ እንገዛለን

እያሉ ልጁን እና ቤተሰቡን ለማብሸቅ ይዘፍናሉ፡፡ ይህን ዘፈን ሙሽራ መጥቶ ሙሽሪትን ከቤት እስከሚወስድ ድረስ እየዘፈኑ ሙሽሪትን ያፅናናሉ፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ለማግባት ሲሄድ ሰርገኞቹ ሙሽራውን ከበው በሚዜዎቹ አማካኝነት ሙሽራውን ካዘጋጁት በኂላ በእናት እና አባቱ እንዲሁም በሽማግሌዎች እንዲህ በማለት ይመርቁታል፡፡

6 *Hayya duree hoomaa hoofee*

*Hadurree billachuu*

*Yaa galaana shiishii*

*Ni dhuffee hiriyyaan koo*

6 ሄደህ በሰላም ተመልሰህ ግባ

ተናግረህ እውነትን አግኝ

እኛን እንዳስደሰትከን አንተም ተደሰት

ብዛ፣ ክበር ዘርን አግኝ

በሰላም ተመልሰህ ግባልን

በማለት ለልጃቸው ያላቸውን ምኞት ይገልፃሉ፡፡ሚዜዎቹም ከሰረገኞች ጋር በመሆን ወደ ሙሽሪት ቤት ሙሽራውን የሚያስደስት ዘፈን እየዘፈኑ ይሄዳሉ፡፡ ዘፈኑም እንዲህ ነው፡፡

7 *Hayya duree hoomaa hoofee*

*Hadurree billachuu*

*Yaa galaana shiishii*

*Ni dhuffee hiriyyaan koo*

7 ይኸው በዝታን እየመጣን ነው

ፊት ለፊት እየመራው ከኋላዬም በዝታው

ጓደኞቼ ከእኔ ጋር ናቸውና አልፈራም፡፡

እባክህ ሆዴ ደስ ይበልህ አትረበሽ

እያሉ ይዘፍናሉ፡፡ ሰርገኞች እየተቀባበሉ የሙሽሪት ቤት እስኪደርሱ ድረስ ይዘፍናሉ፡፡ የሙሽሪት ቤት ሲደርሱ ደግሞ የሙሽሪት ጓደኞች በሩን ይዘው ሙሽራው ወደ ውስጥ እንዳይገባ

ይከለክሉታል፡፡ ይህ <<Balbala qabii>>(በሩን መያዝ) በመባል ይታወቃል፡፡ከበሮቸውን እየደለቁ እንዲህ ይዘፍናሉ፡፡

8 *Yaa garaa koo ciisii*

*Yaa ulee luugama gaangoo*

*gurbaa dhala hanaanqoo*

*Hin kennu balbala abbaako*

8 የበቅሎ ሉጋም እና አለንጋ

አንተ ልጅ ሆይ

የአባቴን በር አላስደፍርም)

በማለት እንደ አካባቢው ባህል ሙሽራው ብር እስኪሰጣቸው ድረስ እየተቀባበሉ በማብሸቅ ይዘፍናሉ፡፡ ሙሽራው ብሩን ከሰጣቸው በኋላ ከሰርገኞቹ ጋር ወደ ውስጥ እንዲገባ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ወደ ውስጥ ገብተው በልተው ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ የሙሽሪት እናት እና አባት እንዲህ በማለት ይመርቋቸዋል፡፡

9 *Qabattani aaga qabadhaa*

*Dubbadhaa dhugaa argadhaa*

*Dhaqqeefi cidii ta'aa walqabadha*

*Marga ta'aa lafa huwwisaa*

*Handoode kormaa ta'aa*

*Bonaaf ganna lalisa*

*Ibidda tuluurraa ta'aa*

*Dubaaf fuunduratti ifaa*

9 ተያይዛችኋልና መልካምን ያዙ

ተናግራችሁ እውነትን አግኙ

ወተት እና ማለብያው ቅል ሁኑ

ጭቃ እና ጭድ ሁኑ

ተያያዙ

ሳር ሁኑ ምድርንም ሸፍኗት

ከዋክብትም ሁኑ ሰማይን ሸፍኗት

በጋ እና ክረምት ሁሌም ለምልሙ

የተራራ ላይ እሳት ሁኑ

ፊት እኍላችሁ በብርሀን ይሞላ)

በማለት ሙሽሪት እና ሙሽራውን ይመርቋቸዋል፡፡ የዚህ ምርቃት ዋናው መልዕክት እንዲስማሙ እና አንድ እንዲሆኑ እንዲሁም ዘራቸው እንዲበዛ መመኘትን ያመለክታል፡፡ ልጅትን ሙሽራው ከቤት ይዟት ሲወጣ የሙሽሪት ጓደኞች እና ጎረቤቶች "Gundoo Booree"(ትንሽዬ ሰፌድ የምትመስል ነገር ) በእጃቸው ይዘው እየዘፈኑ ይሸኛሉ፡፡ ሲዘፍኑን በዚህች"Gundoo Boree" በምትባል ሰፌድ መሳይ ስፌትን እየዞሩ ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በሚዞሯት ስፌት እያስመሰሉ ሙሽራውንም ሰለሚሰድቡት ነው፡፡ በመቀጠል ሙሽሪትን እስከተወሰነ ቦታ ከሸኟት በኍላ ይመለሳሉ፡፡

## 3.2.1 ከመቼት አንፃር

የነቀተኒ የሰርግ ስነስርዓት የተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ያለው ስነስርዓት ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ የነቃተኒ የሰርግ ስነስርዓት የሚከወነው በጥር ወር ነው፡፡ ይኸውም የሚሆንበት ምክንያት በዚህ ወር ማህበረሰቡ አንድ ማህበራዊ እውነታ አለው፡፡ ይኸውም በዚህ ወር ወይም ወቅት እህል (ሰብል) የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ ነው፡፡ ሰርግ ለመሰረግ እህል እና ሌሎች ወጪዎች የሚወጡበት ወቅት በዚህ ወር ነው፡፡

አንድ ቤተሰብ ሰርግ ለመሰረግ ቢያንስ 4 እና ከዛ በላይ ኩንታል የእንጀራ እህል ያስፈልገዋል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች ይኖራሉ፡፡ ታድያ ሰርግ ለመሰረግ ያሰበ ቤተሰብ ይህን ሰብል የሚደርስበትን የጥር ወር መጠበቅ ግዴታው ነው፡፡አንድም እህሉን ለሰርጉ እንጀራ ሲጠቀሙበት ሁለት ደግሞ አውጥቶ ወደ ገበያ በመሸጥ በምትኩ ዘይት እና ለሰርግ የሚያስፈልጉትን ቅመማ ቅመሞች ይገዙበታል፡፡ በዚህም ምክንያት የጥር ወር ለዚህ የሰርግ ስነስርዓት በብሔረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ወቅት ነው፡፡

ቤተሰብ ማለትም የልጁ እና የልጅቱ ቤተሰብ ለጋብቻ ከተስማሙ የመጀመሪያው ግብዣ የሚሆነው በልጅት ቤተሰብ ቤት ነው፡፡ የዚህም ምክንያት የልጅት ቤተሰብ ለሽማግሌዎች ያላቸውን ከበሬታ ለመግለፅ፣ እንዲሁም ልጁን እና ቤተሰቡን በቤታቸው መጥራት ደግሞ ከዚህ በኋላ ባዳ አለመሆናቸውን እና አንድ መሆናቸውን ለማመልከትም ጭምር ነው፡፡ በዚህ በልጅቱ (በታጨችው) ቤተሰብ ቤት የሚሆነው ግብዣ ከሰአት (ከ6 ሰዓት በኋላ) ነው፡፡ ምክንያቱም ትልቅ እና ስምን ለማስጠራት የሚደረግ ግብዣ ስለሆነ ለመዘገጃጀት እና ለግብዣው የሚያስፈልገውን ሁሉንም ነገር በዕለቱ ጠዋት ስለሚያከናውኑ ነው፡፡ከግብዣው በኋላ ሁለቱም ቤተሰብ ለሰርጉ መዘገጃጀት ይጀምራሉ፡፡

## 3.2.5 ከሚና ክፍፍል አንፃር

የነቀተኒ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ላይ የሚከናወኑ ክዋኔዎች የተለያየ አይነት የሚና ክፍፍል አላቸው፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ ብዙ ሰዎች የሚሳተፉ ቢሆንም በዋነኝነት የሙሽሮች ቤተሰብ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ፡ የሙሽራው አባት ደብዳቤውን በመፃፍ ከሙሽሪት ቤተሰብ እሺታን ካገኘ በኋላ ሽማግሌዎችን የማሰባሰብ ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ለሰርጉ የሚያስፈልገውን ሰንጋ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ፈላልጎ መግዛትም የሙሽራው አባት ሀላፊነት ነው፡፡ በተጨማሪም ለእድሩ በማሳወቅ ድንኳን ወይም ዳስ እድርተኞቹ እንዲተክሉለት ያደርጋል፡፡ የሚመጣውን እንግዳ ቦታ ቦታ በማስያዝ እድርተኞች እና ጎረቤት ሀላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ ሙሽራው በበኩሉ ሚዜ የሚሆኑለትን ሰዎች ወይም ጓደኞች በመምረጥ ሀላፊነቱን ይወጣል፡፡ ልብስም ይገዛዛል፡፡ በተጨማሪም ሙሽራ በመሆንም ሰርጉን ያደምቀዋል፡፡ የሙሽራው እናት በበኩሏ ለሰርጉ የሚሆን ከቤት ውስጥ ከጎረቤቶቿ ጋር በመሆን ታዘጋጃለች፡፡ ለምሳሌ ፡- ጠላ ማዘጋጀት፣ ጠጅ መጣል፣ እንጀራና ዳቦ ማዘጋጀት፣ እና የመሳሰሉትን ታዘጋጃለች፡፡ በተጨማሪም ከባል ጋር በመሆን የሚጠሩ ሰዎችን ይመርጣሉ፡፡የሙሽራው ጓደኞች እና ወዳጆች የሰርጉ ቀን እስኪደርስ በቤት

በመገኘት በጭፍራ በማድመቅ ሙሽራውን ያስደስቱታል፡፡ ሽማግሌዎች በበኩላቸው በሁለቱ ቤተሰብ መሀል በመሄድ ጉዳይ ማስፈጸም፤ በምርቃት ወቅት መመረቅ እና የመሳሰሉትን በመፈፀም የስራ ድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡የሙሽሪት ቤተሰብም ተመሳሳይ ነገር ይፈፅማሉ፡፡ ሙሽሪት በበኩሏ በጓደኞቿ አማካኝነት ልብስ ታዘጋጃለች፡፡ እንዲሁም እናቷ የምትሰራውን ስራ በመስራት እናቷን ታግዛለች፡፡

## 3.2.4 ከቁሳቁስ አንፃር

Itille (ቆዳ):-‹‹ Itille›› ወይም ቆዳ በመባል የሚታወቀው ከሰንጋ በሬ ታርዶ የሚገፈፍ ቆዳ ነው፡፡ ይህ ቆዳ ከታረደው በሬ ከተገፈፈ በኋላ ቆዳ በሚፍቁ ሰዎች ተፍቆ ለመኝታ እንዲያገለግል ተደርጎ ይሰራል፡፡ ይህ ቆዳ ሙሽሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ጫጉላ ቤት ውስጥ አብረው የሚተኙበት ነው፡፡ ጫጉላ (Godoo) ለሁለቱ ሙሽሮች የሚዘጋጅ ትንሽዬ ቤት ሲሆን ከላይ ሳር (ገለባ)፣ ግድግዳውን በቅጠላ ቅጠል ሽምጥጠው ነው የሚሰሩት፡፡ጥሩ ሽታ ያላቸውን ቅጠላ ቅጠልም በ Godoo (ጫጉላ) ቤት ውስጥ ያስገባሉ፡፡ ይህ ቆዳም እዚሁ ጫጉላ ቤት ውስጥ ከስር ቅጠል ከተረበረበ በኋላ ቆዳውን ከላይ ያደርጉበታል፡፡ ሙሽሪት እና ሙሽራውም እዚህ ጫጉላ ቤት ውስጥ የመጀመሪያ ግንኙነታቸውን ያደርጋሉ፡፡ ‹‹(ቆዳ) ለሙሽራው ምቾት እንዳይሰማውና እንቅልፍ እንዳይወስደው ነው፡፡ ምክንያቱም ቀኑን በሙሉ በጭፍራ እና ወዲህ ወድያ እያሉ ስለሚውሉ የተመቻቸ ፍራሽ ካገኘ ሙሽራው ስራውን ዘንግቶ ሊያንቀላፋ ይችላል፡፡ እናም ሙሽራውን የሙሽሪትን ክብረ ንፅህና መውሰድ አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ካቃተው ሙሽሪት ትታው መሄድ ትችላለች፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ሙሽራው የአክስት ወይም የአጎት ልጅ ከሌለው ነው፡፡ ሙሽራው የልጅቱን ክብረ ንፅህና መስበር ካልቻለ የሙሽራው ዘመድ የሆነው (Jabbi hootu) የአክስቱ ልጅ ብቻ ካለ ሙሽራውን በመወከለ ከሙሽሪት ጋር ይተኛል፡፡ ለዚህም ነው ሙሽራው እንቅልፍ እንዳይጥለው በጫጉላ ቤት ውስጥ ቆዳ ላይ መተኛት ያለበት፡፡

Gundoo Boore (ትንሽዬ ሰፌድ) ከስንደዶ እና ከአለላ የምትሰራ ሰፌድ የምትመስል ናት፡፡ የተለያየ መልክ አላት፡፡ እናም በጣም የምታምር ናት፡፡ የሙሽሪት ጓደኞች የሚያዘጋጇት ሲሆን ዋናው አላማውም የሙሽራውን የአክስት ልጅ (Jabbii hootu) ለማብሸቅ ነው፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሙሽራው የሙሽሪትን ድንግልና መውሰድ ካቃተው ሙሽራውን በመወከል ከሙሽሪት ጋር የሚተኛው ይህ የሙሽራው የአክስት ልጅ ነው፡፡ እናም ይህን ልጅ የሙሽሪት ቤተሰብ በዘፈን እየዘፈኑ ያበሽቁታል፡፡ የአክስት ልጅም ይህ እንደሚሆን ስለሚያውቅ የሙሽሪት

ቤት ሲሄድ በር ላይ ነው የሚቀመጠው፡፡ ወደ ውስጥ አይዘልቅም፡፡ የሙሽሪት ጓደኞችም ስያበሽቁት ባይናደድም እንደተናደደ መተወን ይኖርበታል፡፡ የሙሽሪት ጓደኞች የሙሽራውን የአክስት ልጅ ለማብሸቅ ከሚጠቀሙበት አንዱ መንገድም ይኸው (Gundoo boore) ነች፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ከቤቱ ወደ ቤቱ ይዞ ሲሄድ የሙሽሪት ጓደኞች ይህቺ<< Gundoo boore >>የተባላችውን ይዘው መሀል ላይ በማስገባት እያዞሯት ይዘፍናሉ፡፡ ይህቹን<<Gundoo boore>> የሙሽራው የአክስት ልጅ እነዚህን እያዞሩ የሚዘፉኑ ሴቶችን ጥሶ በመግባት መውሰድ አለበት፡፡ አለበለዚያ ግን እያዞሩ እሱን መስደቡን ይቀጥላሉ፡፡ የሙሽራው የአክስት ልጅ(Jabbii hootu) ፈርቶ ፡፡<<Gundoo boore >>ሳይወስድ ዝም ብሎ ከሄደ ሰርገኞቹ ከሄዱ በኋላ ሲዞሩ እና ሲዘፍኑ የነበሩ ሴቶች በንቀት ከኀላው ወርውረው ይሰጡታል፡፡ ይህቺ ሌላኛው ጥቅም ሙሽራው የሙሽሪትን ማህተበ ድንግልና ሲያፈርስ የሚፈሰውን ደም በነጭ ነጠላ በመያዝ በዚህች ላይ በማድረግ የምስራቹን ያበስሩበታል፡፡‹‹Gundoo boore›› የሙሽሪትን ንፅህና መስካሪ ነች፡፡

Okkotee cabaa (ዋዳት)፡- ይህ እቃ ከአፈር የሚሰራ ሸክላ ሲሆን ከላይ ክፍት ነው፡፡ ይህም የሚያገለግለው እጣፋንታን ለማየት ገብሶቹን በሚዘሩበት ወቅተ በዚህ "okkotee cabaa" ውስጥ ያኖሩታል፡፡ ገብሱን በውሃ ከነከሩ በኋላ በዚህ ዋዳት ውስጥ በመሆኑ ገብስ ለማብቀል ስለሚያመች ይህን ዋዳት ይጠቀሙበታል፡፡

Ulmaayi (ኡልማይ)፡- በጣም ደስ የሚል ሽታ ያለው የቅጠል አይነት ነው፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ለመውሰድ ሲሄድ በእጁ ይዞት ይሄዳል፡፡ አንድም የሙሽሪት ቤተሰብ ቤት ላይ በመሰካት ለቤተሰቡ ያለውን ክብር ይገልፃል፡፡ ቅጠሉ መዐዛው የሚማርክ በመሆኑ የሙሽሪትን ቤተሰብ መውደዱን ለመግለፅም ይህን ቅጠል በመያዝ ወደ ሙሽሪት ቤት ይመጣል፡፡››በማለት የማህበረሰቡ ነዋሪ ኦላኒ ፈይሳ ተናግረዋል፡፡ (ኦላኒ ፈይሳ፣ 02/02/2014

ዋንጫ፡- ይህ ከከብቶች ቀንድ የሚሰራ ለመጠጥ የሚያገለግል እቃ ነው፡፡ በባለሞያ ከቀንድ የሚሰራው ይህ ዋንጫ ሙሽሮች የሚቀርብላቸውን መጠጥ የሚጠጡበት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ይህ እቃ ትልቅ ክብር ያለው በመሆኑ ሙሽሮች በዚህ እቃ ይጠቀማሉ፡፡ መሶብ፣ መሶበ ወርቅ ፣ ሰፌድ፣ ብረትድስት፣ ሳጥን፣ ጠረጴዛ፣ ጀግ፣ እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች በዕለቱ ሰርግ ላይ ለሙሽሮች በስጦታ መልኩ የሚመጡ ናቸው፡፡፡ ሙሽሮች ጎጆ ወጪ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ የተለያዩ ቁሳቁሶች በስጦታ መልኩ ይሰጣሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ የሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ ያሉት ቁሳቁሶች ትውፊታዊ ይዞታ ያላቸው እና በማህበረሰቡ ዘንድም አሁን ላይ እየተረሱ መሆኑን ኦላኒ ፈይሳ ባደረግንላቸው ቃለ-መጠየቅ መሰረት ነግረውናል፡፡

### 3.2.3 ከአልባሳት አንፃር

በነቀተኒ የሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ የተለያዩ አይነት አልባስ ይለበሳሉ፡፡ ከሙሽሮች አንስቶ እስከ ሰርገኞቹ የተለያየ ልብስ ይለብሳሉ፡፡

ሙሽራው የሚለብሰው ሙሉ ሱፍ ሲሆን፣ ሱፍ ከጉልበቱ ወረደ ይልና ከስር ሰፋ የሚል ሱሪ ነው፡፡ ጫማው አስኮ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የጫማው መልክ ሙሉ ለሙሉ ነጭ ነው፡፡ ይህ ጫማ ትንሽ ተረከዝ ያለው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙም አይስተዋልም፡፡ ሙሽራው ፀጉር ካለው ጎፈሬ ያደርግና ለሰርጉ ይዘጋጃል፡፡ ሚዜዎቹ ደግሞ ተመሳሳይ አይነት አለባበስ ሆኖ ከሙሽራው በመልኩ የሚለይ ነው፡፡ ለምሳሌ የሙሽራው ሱፍ ነጭ ከሆነ የሚዜዎቹ ደግሞ ጥቁር ይሆናል፡፡

ሙሽሪት ደግሞ ከጥጥ ፈትል የሚሰራ ሙሉ ነጭ ልብስ ትለብሳለች፡፡ የምትጫማው ጫማ ልክ እንደ ሙሽራው ሁሉ አስኮ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ተረከዝ የለውም፡፡ ሙሽሪት ፀጉሯን ወደ ኋላ አበጥራ ማስያዝ፣ አልያም ደግሞ ፀጉሯን በባህላዊ መልኩ መሰራት ትችላለች፡፡ የሙሽሪት እና የሙሽራው ቤተሰብ የፈለጉትን አይነት ልብስ መልበስ ይችላሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን አባት ሙሉ ነጭ ይለብስና ጋቢ ከላይ ይደርባል፡፡

ሰርገኞች በበኩላቸው ወንጨሬ የሚባል የልብስ አይነት ይለብሳሉ፡፡ ወንጨሬ እስከ ጉልበት ሰፋ ይልና ከጉልበት በታች ጥብቅ የሚል የልብስ አይነት ነው፡፡ ወንጨሬ ከለበሱ በኋላ ከላይ ጋቢ ጣል ያደርጋሉ፡፡ ሌሎች በሰርጉ ላይ ተጠርተው የሚታደሙ ታዳሚዎች የፈለጉትን የልብስ አይነት ለብሰው መታደም ይችላሉ፡፡

ሙሽሪት እና ሙሽራው ነጭ የሚለብሱት እስከ ሰርጉ ዕለት እራሳቸውን ጠብቀው ስለቆዩ በተለይ ሙሽሪት ጋብቻው መጀመሪያዋ ከሆነ ክብሯን ጠብቃ እስከ ጋብቻዋ በመኖሯ ንፅህነዋን ለመግለፅ እና ለማመልከት ነው፡፡ ነጭ ንፅህናን ይወክላልና፡፡

ወንድ (ሙሽራው) ነጭ መልበሱ ያን ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ ብቻ ለሙሽራውም ቢሆን ትርጉሙ አንድ አይነት ነው፡፡

ሙሽራውም የሙሽሪትን ቤተሰብ ስያለብስ (ለሙሽሪት አባት ጋቢ ለእናቷ ደግሞ ነጠላ ወይም ቀሚስ ይሰጣቸዋል፡፡ ለሙሽሪት በዕለቱ በሰርጉ ላይ የሚታደሙ ዘመድ እና ወዳጆቹ ነጠላ እና ሌሎች አልባሳትን በስጦታ መልኩ ሊሰጧት ይችላሉ፡፡

## 3.2.2 ከድርጊት አንፃር

### 3.2.2.1 ቅድመ ክንውን

የነቀተኒ የሰርግ ስነስርዓት ከመከወኑ በፊት ዝግጅት ወይም ቅድመ ክንውን ይኖራል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ ልጁ ዕድሜው ለጋብቻ ከደረሰ በኋላ ማግባት የሚፈልጋትን ሴት በተለያየ መንገድ ሊያያት ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሌሎች የሰርግ ቦታዎች ላይ ስትጨፍር፣ ውሀ ለመቅዳት ወንዝ ስትወርድ፣ ገበያ ስትሄድ እና በመሳሰሉት መንገድ ልጅቷን ሊያይ ይችላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የወደዳትን ሴት በቅርበት ለማግኘት እንደ እንግዳ ወይም በሌላ ምክንያት ቤታቸው በመሄድ ያያታል፡፡

በዚህ መልኩ ስለ ወደዳት ልጅ በደንብ ከተረዳ በኋላ ለቤተሰቡ ለልጅት ቤተሰብ ደብዳቤ እንዲልኩ ይጠይቃል፡፡ ቤተሰቡም ጥያቄውን ተቀብለው ስለ ልጅት ቤተሰብ ማንነት በደንብ ከተረዱ በኋላ በኑሮ ደረጃ የሚመጣጠኑ ከሆነ ደብዳቤ ይልካሉ፡፡ የልጅት ቤተሰብ ዝቅተኛ የኑሮ አኗኗር ቢኖራቸው እና የልጁ ቤተሰብ ደግሞ ሀብታም ከሆነ የልጁ በተሰብ ምንም ያህል ልጁ ልጅትን ቢወዳትም ደብዳቤ የማይልኩበት ሁኔታም ይኖራል፡፡

በዚህ በነቀተኒ የሰርግ ስነስርዓት ላይ አንድ ወንድ ልጅ የወደዳትን ልጅ ለቤተሰብ የሚነግርበት ሁኔታ አልፎ አልፎ እንጂ እምብዛም አይስተዋልም፡፡ የወዳደዳት ልጅ በቤተሰቡ ካልተወደደች ወይም የእሷነም ቤተሰብ የልጁ ቤተሰሰብ ካልተመቿቸው ልጁ የወደዳትን ልጅ ላያገባ ይችላል፡፡ይህ ማለት ለሰረግ የሚተጫጨትን ወንድም ሆነ ሴት የሚመርጡት ቤተሰቦቻቸው ናቸው ማለት ነው፡፡

በቤተሰቡ አማካኝነት ስለ ልጅቷ ቤተሰብ ጥናት ከተደረገ በኋላ ለልጃቸው የምትሆን እንስት ለጋብቻው ትመረጥና የልጁ ቤተሰብ ለልጅቷ ቤተሰብ ደብዳቤ ይልካል፡፡ የልጅት ቤተሰብም ልክ እንደ ልጁ ቤተሰብ በተመሳሳይ መልኩ ስለቤተሰቡ ጥናት ያደርጋል፡፡ ከተስማሙ በሳምንት ጊዜ ውስጥ የእሺታቸውን ደብዳቤ ይመልሳሉ፡፡ በመቀጠልም የልጁ ቤተሰብ ወደ ልጅት ቤተሰብ ሽምግልና ይልካሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የልጁ አባትም ከሽማግሌዎች ጋር ወደ ቤተሰቧ ይመጣል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዕለት ስለ ሰርጉ ሁኔታ እና የሰርጉን ቀን ለመወሰን ሁለቱ ቤተሰብ ይወያያሉ፡፡

በልጅት ቤተሰብ መካከል የተገኙት ሽማግሌዎች እና የልጁ አባት ስለ ቀኑ ይወያያሉ፡፡ የሁለቱ ቤተሰብ ሀሳብ ካልተገጣጠመ ሽማግሌዎች መሀል ገብተው እንዲስማሙ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም

በአንድ ሀሳብ ከተስማሙ በኋላ ‹‹Milki Ilaallanna›› (እጣፈንታ መወሰን) ተቀጣጥረው ይለያያሉ፡፡

## Milki Ilaallanna (እጣፋንታ ማየት)

በዚህ የነቀተኒ የሰርግ ስነስርዓት እጣፈንታን ማየት እንደ ግዴታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሁለቱ ልጆች የወደፊት እጣፈንታ መልካም ይሁን መጥፎ ያያሉ ፡፡ ይህንም የሚያደርጉት ስለ ሁለት የወዳፊት ኑሮ በመጨነቅ እና መልካም እንዲገጥማቸው በማሰብ ነው፡፡

ይህንንም እጣፈንታ የሚያዩት ሁለት የገብስ ፍሬዎች በውሀ ውስጥ በመዘፍዘፍ ነው፡፡ እነኚህ ሁለት የገብስ ፍሬዎች ከቀናት በኋላ ሁለቱም ፍሬዎች በስርዓት ከበቀሉ ትዳራቸው የሰመረ ነው፡፡ በማለት ማህበረሰቡ ያምናል፡፡ ነገር ግን የገብስ ፍሬዎቹ በስርዓት ካልበቀሉ እና እክል ከገጠማቸው ትዳራቸው መልካም እንደማይሆን እና የተስተካከለ ሕይወት አይኖራቸውም ብለው ያምናሉ፡፡

ስለዚህም ችግሩ ምን እንደሆነ እና እንዴት ማስተካከል እንዳለባቸው ለማወቅ አዋቂ ቤት (ጠንቋይ ቤት) በመሄድ ችግሩን ለማወቅ ይሞክራሉ፡፡ ጠንቋዩም ነገሩን ተረድቶ መፍትሄ ያለውን ነገር ይነግራቸዋል፡ የልጆች ቤተሰብም ከአዋቂ ቤት (ጠንቁይ) የታዘዙትን በመፈፀመ የልጆቻቸው ትዳር እንዲሰምር ደፋ ቀና ይላሉ፡፡

እጣፈንታን ማየት ለዚህ በጃርደጋ ጃርቴ ለሚኖር ማህበረሰብ ትልቅ ትርጉም ያለው እና ትልቅ ቦታም የሚሰጠው ነው፡፡ አንድ ጊዜ የልጅት ቤተሰብ የልጁን ቤተሰብ ካልወደዱ ነገር ግን እምቢ ማለት ከፈሩ በዚህ ሁለት የገብስ ፍሬዎች ላይ የፈላ ውሀ በመጨመር እንዳይበቅሉ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የተጀመረው የትደር ጉዞ ይቀጫል፡፡

እጣፈንታ የማየት ስነስርዓት ተከናውኖ እጣፈንታው መልካም ከሆነ ለሰርጉ ቀን ተቆርጦ ዝግጅት ይጀምራል፡፡ ሴቶች ለሰርጉ የሚውለውን የእንጀራ፣ የዳቦ፣ የጠላ፣ ወዘተ. እህልን ለማዘጋጀት ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ ወንዶችም ለእርድ የሚሆኑ ከብቶችን በመመረጥ እና በመግዛት ያዘጋጃሉ፡፡

ሰርጉ ለመድረስ ሁለት ሳምንታት ሲቀረው በሁለቱም ቤተሰብ ቤት ጭፍራ ይጨፍራሉ፡፡ ይህም<<Jala bulti>> በመባል ይታወቃል፡፡ እስከ ሰርጉ ዕለትም ይህ ጭፍራ ይቀጥላል፡፡

### 3.2.2.2 በክዋኔው ወቅት

በነቀተኒ የሰርግ ዕለት የተለያዩ ድርጊቶች እና ሰርአቶች ይፈፅማሉ፡፡ ሙሽሪት በዕለቱ በጓደኞቿ አማካኝነት ስትዋብ ትቆያለች፡፡ በሙሽራውም ዘንድ እንዲሁ በሚዜዎቹ ሲዋብ ይቆያል፡፡ በሁለቱም ቤተሰብ ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ ክንውን ይከናወናል፡፡ የተዘጋጀው ጠላ እና ጠጅ ለታዳሚዎች ለማቅረብ ምቹ በሚሆንበት ቦታ ይቀመጣል፡፡ እንዲሁ የተዘጋጁት የተለያዩ አይነት ምግቦችም ቦታቸውን በማስያዝ የእንግዶቹን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ የሙሽሪት ቤተሰብ እንግዶቻቸውን እያስተናገዱ የሙሽራውን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ ሙሽሪትም አምራ አሸብርቃ በሚዜዎቿ ታጅባ ቁጭ ትላለች፡፡

ሰዓቱ ደርሶ ሙሽራው በሰርገኞች ታጅቦ የሙሽሪት ቤተሰብ ቤት ይደርሳል፡፡ ከሙሽሪት ወገን ያሉ ሰዎችም የተለያየ ይዘት ያላቸውን ዘፈኖች በመዝፈን ሙሽራውን ወደ ቤት እንዳይገባ ያበሽቁታል፡፡ ሙሽራውን ብቻ ሳይሆን ሚዜዎችንም በመስደብ ያበሽቃሉ፡፡ ሚዜዎችም በአጠፋው ዘፈናቸውን ከሰርገኞች ጋር ሞቅ አድርገው በመዝፈን ያስደስቷቸዋል፡፡ በደንብ ካልዘፈኑ እና የሙሽሪት ቤተሰብን በሚገባ ካላወደሱ በሙሽሪት ወገን ያሉ አቀንቃኞች ይህን ድርጊታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ሙሽራው ሙሽሪት ቤት ሲደርስ በእጁ **የተለያዩ** ስጦታዎች ለቤተሰቧ ይዞ ይሄዳል፡፡ ይህም "Uwwisaa" በመባል ይታወቃል ፡፡ "Uwwisaa" ማለት ለሙሽሪት እናት እና አባት የተለያዩ አልባሳትን ይዞ በመሄድ እግሮቻቸው ላይ ወድቆ እየሳመ ማልበስ ነው፡፡ በዚህም ጉልበታቸው ላይ በመውደቅ ለሙሽሪት ቤተሰብ ያለውን ክብር ይገልፃል፡፡ ከዚህ በኋላ በቤተሰቦቻቸው እና በሽማግሌዎች ከተመረቁ በኋላ ሙሽሪት ታጅባ ለሙሽራው ትሰጣለች፡፡ ሙሽራውም ሙሽሪትን ከወሰደ በኋላ የሽማግሌዎችን ምርቃት ተቀብለው አብረው በልተው ይጠጣሉ፡፡ በመቀጠልም ጭፈራው እንደገና ይደራል፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ከቤት ይዞ ሲወጣ እልልታ እና ጭፍራው ሞቅ ይላል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ መሳሪያዎች ተኩስ ድምፅም ይሰማል(የደስታ)፡፡

ሙሽራው ሙሽሪትን ወደ ቤተሰቡ ይዞ ሲገባ የልጁ ቤተሰብ በጉጉት ሲጠባበቁ በመቆየታቸው በር ላይ ጠብቀው እየዘፈኑ እልል እያሉ ይቀበሏቸዋል፡፡ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታም በአጃቢዎች በዘፈን እና በእልልታ እየታጀቡ ይቀመጣሉ፡፡ ከበሉ ከጠጡ በኋላ እነዚህም በተመሳሳይ መልኩ የሽማግሌዎችን ምርቃት ተቀብለው ሙሽሪትም ለሙሽራው ቤተሰብ ያላትን አክብሮት ለመግለፅ ጉልበታቸውን እየሳመች ምርቃት ትቀበላለች፡፡ የዛው ዕለት ምሽትም ሙሽራው እና ሙሽሪት ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ አልጋ ለሁለት ይጋራሉ፡፡

### 3.2.2.3 ድህረ-ክዋኔ

ከሰርጉ ዕለት በኋላ ሙሽራው እና ሙሽሪት የትዳር መንገዳቸውን ጉዞ በመጀመር አንድ ላይ መኖር ይጀምራሉ። በሶስተኛው ቀን መልስ ከተጠራሩ በኋላ የሰርጉ ፍፃሜ በሙሽሪት ቤት ሙሽራው በግ ይዞ በመሄድ እና በጉን አርዶ ለማዘጋጀት ከሚዜዎቹ ጋር ሽር ጉድ ይላል። በጉን እርደው አዘጋጅተው ከመገቡ በኋላ በሽማግሌዎች ተመርቀው ጭፍራው ይደራል። ሙሽራው በጉን አርዶ የሚመግብበት ምክንያት ለቤተሰቡ ያለውን ክብር ለመግለፅ እና በሙሽሪት (በሚስቱ) ደስተኛ እና የትዳር ጉዞውን መውደዱን ለመግለፅ ነው።

# ምዕራፍ አራት

## 4.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት ትኩረቱን ያደረገው በ ኦሮሚያ ክልል፣ሆሮጉድሩ ወለጋ ዞን፣ጃርደጋ ጃርቴ ወረዳ ውስጥ በሚከወነው የነቀተኒ የጋብቻ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር መተንተን ላይ ነው።ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የነቀተኒ የሰርግ ስረአትን ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ምን እንደሚመስል እና ያለውን ተዛማጅነተ ለመቃኘት ሞክሯል።

ይህ የነቀተኒ የሰርግ ስነ ስረአት በዚህ በጃርደጋ ጃርቴ አከባቢ ለሚኖሩ ማሕበረሰብ የላቀ እና ተወዳጅነት ያለው የሰርግ ስነ ስረአት መሆኑን አጥኚው ከአጠናው ጥናት መረዳት ችሏል።ይህ የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስረአት በሚከወንበት ወቅት ማሕበረሰቡ ትውፊታዊ ድረሰጊቶችን በመጠቀም ስለፍቅር፣ስለትዳርና ስለቃልኪዳን የመሳሰሉት መልክቶችን በተለያየ መንገድ ሲያስተላልፍ ኖሯል። ለምሳሌ፦በሚለብሱት አልባሳት፣በሚጠቀሙበት ቁሳቁስ፣በሚጨፍሩት እና በሚዘፍኑት ዘፈን፣በምርቃቶች እና ንግግሮች እና በመሳሰሉት መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍ ኖሯል።

**አሁን ላይ ግን ይህ ስርዓት እንደ ሃይማኖት፣ ዘመናዊነት** ባመጣቸው ስነ ስርዓቶች **እየተረሳ መምጣቱን** አጥኚው ከአነጋገራቸው የማሕበረሰቡ አካላት በጥናቱ ለማረጋገጥ ችሏል።

## 4.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህ የነቀተኒ የጋብቻ ስነ ስረአት አሁን ላይ ማሕበረሰቡ ትኩረት እየሰጠው እንዳልሆነ አጥኚው በጥናቱ ተረድቷል።የወረዳው የሚመለከተው አካልም ይህን ባህል ትኩረት ሲሰጠው አልታየም።በመሆኑም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባህሉን በመመዝገብ እና በተለያዩ መንገዶች ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ እንዳለበት አጥኚው ተረድቷል።ለምሳሌ፦ ስረአቱን በቴአትር መልኩ በማዘጋጀት ለአከባቢው አልፎም ለሀገሪቱ ማሕበረሰብ የሚያስተዋውቅበት መንገድ ቢመቻች፤እንዲሁም በነቀተኒ የሰርግ ስረአት በሚደገስ ሰርግ ላይ በመገኘት ድርጊቶችን በካሴት ቀርፆ በማስቀመጥ ለሌሎች የማሕበረሰብ ክፍል ማሳየት።በተጨማሪም የባህል ሲፖዝየም በማዘጋጀት እና እንግዶችን በመጋበዝ ባህሉን ማስተዋወቅ ይኖርበታል።ማህበረሰቡም በተለይ ወላጆች ለልጆቻቸው ባህሉን ማስተማር እና ማስወረስ አለባቸው።እንዲሁም ደራሲያን ባህሉን በማጥናት በመፀሀፍ መልኩ ለትውልዱ ቢያሳውቁ ስረአቱ እንዲታወቅ እና እንዳይጠፋ ይረዳል በማለት አጥኚው የመፍትሔ ሀሳቡን ያስቀምጣል።

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1 Abba:- bayyachufaan jeedha sif ha millka'uu nan jeedha.

Jarsa:- sif ha millka'uu bayyadhuu

Abba:- Ulfiaachuufan jedha Ulfadhuu nan jeedha

Jarsa:- Ulfataadha duraanu Ulfaatdhu

Abba:- Wanan isiin bira dhufeef beektanituu gammachuun koo akka gammachuu keessanitii naf lakkoftaanii Ulfinaa gammachukoof akka akka deebii naf kenitanifaan dhufee

Jarsaa:- garii gotee gammachuunke gammachuu keenya. Baga nagaan dhuftee. Hintala eenyuu barbaadde?

2 Abba hintaala:-Baga nagaan dhuftaan seena
Jarsaa 1:-Baga nu ulfeesitaan ulfaadha garuu har'a seenuf hin dhufnee.
Jardaa 2:- lapheen kenyii ala turu jalaateera.
Jarsaa 3:-Amma lapheen keenya ol seenu filatuutii bakkee kana ha teenyuu

3 Abba hintalaa:- noora
Jarsaa 1:- dubiin nu'i itii garakee dhufnee duresee si ga'eera Abban ''eebelu'' gammachuusa siniin ga'u filateera kanaf mana ketii argaamne
Abba hintala:- Gammachichi ananis dabalateetii.

4 *Harmii koo hin baane*

*Ni quuquxe malee*

*Ya haayyooleekoo*

*Laanni koo hin geenye*

*Naquuftani malee*

5 *Yaa hiddi koololee jimmaa*

*Yaa gurbaa osolee ilmaa*

*Haatii kee duutemoo jirti*

*Gurgureetu okkotee binna*

*6 Dhqii nagana gali*

*Dubadhuu dhugaa argadhuu*

*Akka gamanee atiis gammadi*

*Bayyadhu,ulfaadhu qomo argadhuu*

*Nagana debi nuf gali*

7 *Hayya duree hoomaa hoofee*

*Hadurree billachuu*

*Yaa galaana shiishii*

*Ni dhuffee hiriyyaan koo*

8 *Yaa garaa koo ciisii*

*Yaa ulee luugama gaangoo*

*gurbaa dhala hanaanqoo*

*Hin kennu balbala abbaako*

9 *Qabattani aaga qabadhaa*

*Dubbadhaa dhugaa argadhaa*

*Dhaqqeefi cidii ta'aa walqabadha*

*Marga ta'aa lafa huwwisaa*

*Handoode kormaa ta'aa*

*Bonaaf ganna lalisa*

*Ibidda tuluurraa ta'aa*

*Dubaaf fuunduratti ifaa*

## ዋቢ ጽሁፎች


ዘሪሁን አስፋው ፡፡ (2005)፡፡የስነፅሁፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ ፡፡ንግድ ማተሚያ ጅርጅት፡፡

ፋንታሁንእንግዳ ። (1993)።ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ።አዲስ አበባ ። ብረሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።

____________ ። 2009 ። የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ ። አዲስ አበባ ። አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ።

ያለውእንዳወቀ ። (2009) ። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር።አዲስ አበባ ። ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት ።

ፍቃደ አዘዘ ። 1976 ። ትውፊት ምንድነው ? ትውፊት በስነ ፅሁፍ ውስጥ ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሴሚናር የቀረበ ።

አለም እሸቱ ። (1994)።መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ።አዲስ አበባ። ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የልብራል አርትስ ፋካልቲ ህትመት ።

Jaalallii Hayiluu.(2011).Xiinxala fayyadama Afaanii. Asoosama Yaadanii keessatti.

*Yeneenesh Saamu'el.(2010).Qaccessa Sirba Fuudhaafi Heeruma Oromoo Wallaggaa.Anaa Giddaa Ayyaanaa.*

አባሪ



ጮሮርሳ - ባህላዊ ምግብ



ሙሽራው እና ሙሽሪት በዋንጫ እየጠጡ



ክብ ተሰርቶ የሚጨፈር ባህላዊ ጭፈራ



ምርቃት ሲመረቅ



ጮሮርሳ ከመጠጫ ዋንጫ ጋር